“የማይጠቅመውንም፡ባርያ፡በውጭ፡ወዳለው፡ጨለማ፡አውጡት፡በዚያ፡ልቅሶና፡ጥርስ፡ማፋጨት፡ይሆናል።”(ማቴ፡ምዕ፡25፤30)

# መክሊቱ፡የታለ?

አየኻቸው፡ያተረፉትን፤
መክሊታቸውን፡ያልቀበሩትን፤
ወጥተው፡ወርደው፡ያመጡትን፤
እጥፍ፡ድርብ፡ያደረጉትን።
ደስ፡ሲሰኝባቸው፡ጌታቸው፤
ማዕረግ፡እየሰጠ፡ሲሾማቸው፤
በበረከት፡ሲሞላቸው፤
አያሰቀናም፡ይኼ፡ፀጋ፤
ሲታወቅ፡የልፋት፡ዋጋ፤
አይበልጥም፡ወይ፡ከሽሽጋ።

የተራበውን፡ብታበላው፤
የታረዘውን፡ብታለብሰው፤
የታመመውን፡ብትጠይቀው፤
የታሠረውን፡ብትጎበኘው፤
የወደቀውን፡ብታነሳው፤
ያዘነውን፡ብታፅናናው፤
ይኼ፡እኮ፡ነው፡መሠረቱ፤
መነሻ፡ምስጢሩ፡የመክሊቱ፤
የነፍስ፡ስንቅ፡መያዣው፤
ስጋን፡መግደያ፡መሣሪያው፤
አደብን፡መግዣ፡መቆጣጠሪያው፤
ሥራ፡ፈትነትን፡ማባረሪያው፤
ማንነትህን፡ማሳወቂያው፤
የክርስትና፡ሕይወትህ፡መገለጫው።

አንተ፡ግን፡ተወዝፈህ፤
ተረት፡ወደህ፡ወሬ፡ለምደህ፤
ከስንፍና፡ጋር፡ቤትህን፡ሰርተህ፤
መልሰህ፡እኔኑ፡ከሰህ፤
አፍህን፡ሞልተህ፡ስታወራ፤
እንዴት፡አትባል፡የሰው፡ተራ፤
መክሊት፡ቀብረህ፡ስትጣራ፤
ንፍገት፡ይዞህ፡እንዳታጋራ።

በል፡እንግዲህ፡ንሳ፤
ለጥርስ፡ማፋጨቱ፤
ለመጣል፡ወደ፡እሳቱ፤
ለአንተ፡ይኼ፡ነው፡ሽልማቱ፤
ዕድል፡ዕጣህ፡የመክሊቱ፤
የማዕረግ፡ስምህ፡የሹመቱ።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ
ለንደን
መጋቢት፡2001